በፍኖተ ዲሞክራሲ ሬድዮ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ፤ ሕ ዳር 5 ፥ 1997 የቀረበ ሀተታ

# ማን ያውራ የነበረ፥ ኢሕአፓና አገር ወዳድነት (3)

ሀገር የሁሉ ናት በሚል ኢሕአፓ ያካሄደውን ረጅም ትግል ግምገማ ወይም ኢሕአፓና ሀገር ወዳድነት በሚል ርዕስ ትንተና ከመግባታችን በፊት የተያያዘ በመሆኑ የፍልስጤሙ መሪ የያሲር አራፋትን ዕረፍትና የወያኔውን አሳፋሪ መሪ የጀርመን ሀገር ልፈፋ መተቸት እንገደዳለን፡፡ የፍልስጤሙ መሪ በስደተኝነት ደረጃ ተመድቦ የነበረውን የፍልስጤም ሕዝብ ትግል መርተው ማንነቱን በመስዋዕትነት ያስረገጡ ታላቅ ሰው ከመሆናቸው ሌላ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብት የተደረገውን መራራ ትግል በተጨባጭ የደገፉና ከኢሕአፓም ጎን አለምንም ቅድመ ሁኔታ የቆሙ ሰው ነበሩ፡፡ ያሲር አራፋት አሜሪካና እስራኤልን ያክል ያመረሩ ጠላቶች ቢኖሯቸውም፥ የሕዝባቸውን ጥቅም አሳልፈው ከቶም አልሰጡም፡፡ እኚህ ታላቅ ሰው በሞቱበት ሳምንት ውስጥ ደግሞ፥ የቅሌት እናት መለስ ዜናዊ ፥ጀርመን ሀገር ተገኝቶ ከጀርመን እውቀትን እንጂ፥ የገንዘብ እርዳታ አንሻም ብሎ በሀሰት ከርቤ ሲታጠንና፥ ኢትዮጵያን ለአደጋ ያጋለጠውን የብሄረሰብ ፖለቲካ የአፍሪካ ፖለቲካ ገፅታ ነውና ሱዳንም ትቀበለው ብሎና ጠማማ ጎጆ የሰራ፥ ስለ ቤት ስራ ምክር አይለግስ የተባለውን በመፃረር ሲለፍፍ ሰምተናል፡፡ ለሕዝቡና ለሀገሩ የተዋደቀና መከራ የተቀበለ ታላቁ ሰው ያሲር አራፋት በአንድ በኩልና በሌለ ጎን ደግሞ፥ ሌሎች ያቋቋሙትን ድርጅት በሻጥር ነጥቆ ሚሊዮኖች የሞቱላትን ሀገር ያዋረደና ገንጣጥሎ ሊያፈርስ የተነሳ ቡከን ግለሰብ መለስ ወዲ ዜናዊን ስንመለከት፥ ለሕዝብና ለሀገር እየተሰዉ መኖር እየ ሩ መሰዋት ምን እንደሆነ መገንዘብ እንችላለን፡፡ ታሪክ እየሰሩ መታገል ታሪክ ሰርቶ ማለፍን እንማራለን፡፡ ልክ እንደሰማዕታቱ አባት እናቶቻችን!

የኢሕአፓ ሀገር ወዳድነት ሀገርን ከሕዝብ የነጠለ ሳይሆን፥ ኢትዮጵያን ከኢትዮጵያውያን አቀራኝቶ የሁሉም ሀገር ትሆን ዘንድ የሚፈልግ አቋምና አምነት ነበረ፤ አሁንም ነው፡፡ሕዝብን ከሕዝብ የሚለይ ሥርዓት፤አንዱን የበላይ አንዱን የበታች የሚያደርግ ሥርዓት፤ አንዱን በዝባዥ ሌላውን ተበዝባዥ የሚያደርግ ሥርዓትና አገዛዝ በመሠረቱ ሀገር የሁሉም ናት የሚለውን መርህ ተቃውሞ ልዩነትን አፍኖ፥ ብጥብጥን የሚያነግስ ነው፡፡ የትምክህት አባወራዎች ዛሬም ሆነ ትላንት፥ ኢትዮጵያ ወይም ሕዝብ ሲሉ እንደ ታሪካዊው አባባል በ 500 ባይወስኑትም፥ ብዙሀኑን አይጠቀልሉም፡፡ በብሄረሰብ ወይም በሀይማኖት ልዩነት ያደርጋሉ፡፡ ወደ ጠባቦቹ ስንመጣ ደግሞ ከራሳቸው በሄረሰብ ውጪ ሌላው ጨቋኝና ጠላት ተብሎ ተፈርጆ፤ ሥልጣን ሲይዙም፥ ጥቃትና ልዩነት ደርሶበት እንዲኖር የሚያደርጉ ናቸው፡፡ የአፄ ኃይለሥላሴ ኢትዮጵያ ሁሉም ዜጋ በእኩል ሕዝብ አላላም፡፡ እነ መለስ ደግሞ ኢትዮጵያ ማለት ራሱ የሚያማቸው ከመሆኑ በላይ፥ ሕዝባችን ሲሉ /ያውም ለይስሙላ ቢሆንም/ ከክልል አንድ ውጪ አይደለም፡፡ ወደ ኤኮኖሚው መስክ ስንመጣ ደገሞ የፊውዳሉ ሥርዓት ብዙሀኑን ገበሬ ወይም አርሶ አደር በጢሰኝነት ይዞ እያስገበረ ሲያሰቃይና ሲበዘብዝ ነበር፡፡ አንዱ ገባር ሌላው ጌታ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ የሁሉም ዜጋ አልነበረችም፡፡ የኮለኔል መንግሥቱም አረመኔ አገዛዝ፥ ለሰርቶ አደሩ ቆምኩ ቢልም በሰርቶ አደሩ ላብ የተጫወተ የኮታ አስገባሪ በዝባዥ አገዛዝ ነበር፡፡ የወያኔ ሥርዓት ደግሞ፥ መለስና አዜብ ጎላ፤ስብሀትና የወያኔ ተቋማት እየከበሩ ብዙሁኑ የሚሰቃይበት ሥርዓት ነው፡፡ ካፒታሊዝም አሉት ሌላ፤ በባዕዳን በዝባዦች ተመስገነ ተደነቀ፥ ሥርዓቱ ሀገርን የጥቂቶች ከበርቴዎች ሀገረ ያደረገና ብዙሀኑን የሚኮሩባትና በክብር የሚኖሩባት ሀገር እንዳትሆነ ያደረገ ሥርዓት ነው፡፡ኢሕአፓ ይህን ሁሉ ተቃውሞ ለብዙሀኑ ኢትዮጵያ የታገላ እየታገለም ያለ ድርጅት ነው፡፡

ኢሕአፓ መሬት ለአራሹን መብት ለጭቁን ብሄረሰቦች ከሚለው መፈክር ጋር አያይዞ ለዴሞክራሲ የታገለው፥ ሁለቱም ጥያቄዎች በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ የተያያዙ ስለነበሩ ብቻ ሳይሆን፥ ሀገር የሁላችን ትሆን ዘንድ እኩልነት በፖለቲካውም በኤኮኖሚውም መስክ መረገጋጡ ወሳኝ መሆኑን በማመኑ ነው፡፡ የዚህ አቋም ትክክለኛነት ደግሞ በየካቲት 66 አብዮት ተከስቶ ጭቁኖች በጋራ ተነስተው፤ብሄረሰብ ሳይለዩ፤ በሀይማኖት ሳይከፋፈሉ ያደረጉት ቆራጥ ትግል ምስክር ነው፡፡ የትምክህት መሠረቱ ሲመታ የሌላው ክፍፍል ገፅታ አባወራዎች እነ ወያኔ ደግሞ፥ እንደ አሸን ፈሉ፡፡ የጋራ ሀገር ሳይሆን ፍርስራሽን

ፈላጊዎች፡፡ የተባበረ፥ የተወሃደ፥ የጠነከረና በአንድነቱ ፀንቶ የሚኖር ሕዝብ ሳይሆን፥ የተከፋፈለ፥ የተፈረካከሰና የየጎጥ አምባ ገነኖች መጫወቻ የሚሆን ሕዝብ ፈላጊዎች፡፡ እንገነጣጠል ባዮች፡፡ ኢትዮጵያዊነትን እንደራደር ባዮች፡፡ ኢትዮጵያ ልብወለድ ናት ባዮች፡፡ በጥበት ተበክለው የሆነ ሕዝበን እንወድም ባዮች፡፡ ኢሕአፓ፥ እነዚህንም ታግሎ የደም ዋጋ በመክፈል፥ ምን ያህል ለጋራ ሀገር እንደቆመ አስመስከሯል፡፡ ወደፊትም ይህን ከማድረግ ወደኋላ አይልም፡፡ኢትዮጵያ ተከፋፍላ ከሚያይ፥ ኢሕአፓ የግል ሞቱን ይመርጣል፡፡ ያለ ኢትዮጵያ ሕይወት የለውምና፡፡  ዛሬ፥ ኢሕአፓን በሀገር አስገንጣይነት ሊከስሱ የተነሱትን፥ ያኔ ጠባቦችንና ገንጣዮችን ሲታገልና ሲደማ፥የት ነበራችሁ? የሚላቸው በባዶ አይደለም፡፡ ጅብ ካለፈ፥ ጫሂ ውሻዎች ሊተቹኝ ብቃት የላቸውም ሲል ነው፡፡በዝባዥ የኤኮኖሚ ሥርዓቶችን ወይም ምርጫዎችንም በመቃወምና የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ጥቅም በማስቀደም ብዙሀኑ ኢትዮጵያውያን በኩራት ሀገራችን የሚሏት እንድትሆን ታገለ ፡፡ ኢሕአፓ ከደርግ ጋር ያደረገውም መራራ ትግል በፖለቲካውም ሆነ በኤከኖሚው መስክ የዚህ አረመኔ ቡድን ስርዓት ፀረ ሕዝብና የጥቂቶች መሆኑን ስለተገነዘበ ነበር፡፡ አገዛዙ ደም  ያፈስሳል እንጂ፥ ዕድገትን ፤ብልፅግናንና አንድነትን ሊያመጣ አይችልም ሲል ኢሕአፓ የታገለው፥ ሥልጣን  ለእኔ ካልሆነ በሚል ሳይሆን (ሥልጣን ከነበረማ የኢሕአፓ ፍላጎት ደርጉ ሊሾመው አልነበርምን?! ) አገዛዙ ሀገር የሁሉም ናት ብሎ ኢትዮጵያን የሁሉም ሀገር ማድረግ አይችልም ከሚል ዕምነት ነበር፡፡ በሁሉም መስክ ደግሞ ለባዕድ ያደሩ አገዛዞች የሀገርን ሕዝባዊነት ማስከበር እንደማይችሉ በማወቁም ነበር፡፡ የእነ መልሰ አገዛዝ ደግሞ፥ ሳይደብቅ ሀገር ላወድም፤ልዘርፍ፤ ላስገነጥልና ላዋርድ የመጣሁ ነኝ በማለቱ፤ በመሠረቱ መታወቂያው ኢትየጵያዊ ሳይሆን፥ አንድ ብሄረሰብ በመሆኑ፤ ሰይጣን ላመሉ መጽሀፍ ቅዱስ  ወይም ቅዱስ ቆራን ይጠቅሳል ሆኖ፥ አምርሮ የሚጠላትን ኢትዮጵያ፥ አልፎ አልፎ ስሟን  ቢያነሳም፥ ወደደም ጠላም ከፋፋይና ዘረኛ ፖለቲካው ሀገርን የጋራ የሚያደርግ አይደለም፡፡ መቸም ሊሆን አይችልም፡፡

የኢሕአፓ ሀገር ወዳድ አቋም ሕዝብና ሀገርን ያጣመረ በመሆኑ ከእኩልነትና ከዴሞክራሲ ጋርም ሊነጣጠል ከቶም የማይችል ነው፡፡ የሕዝብ እኩልነት ካልተረጋገጠ፥ የጋራ ሀገር ልትኖረን አትችልም፡፡ ኢትዮጵያ ለብዙሀኑ የስቃይና የረሀብ ሀገር ሆና ለጥቂቶች ግን የምድር ገነት ከሆነች፥ የጋራ ሀገር ልትኖረን ከቶም ሊታሰብ አይገባውም፡፡ ፍፁም ዕኩልነት ዛሬውኑ የሚለው ይሳካል ብሎ ኢሕአፓ ባይደናገርም፥ ብዙሁኑን ኢትዮጵያዊ የሚያሰቃይና የጥቂቶችን ምቾት ብቻ የሚያረጋግጥ ሥርዓትን አምርሮ መታገልና ማስወገድ አቋሙና ዕምነቱ ነው፡፡ የጋራ ሀገር ትሆንልን ዘንድ መብታችን መከበሩ ወሳኝ ነውና የተቀማነውን ሀገር ለማስመለስ ከጨቋኝ ሥርዓቶችና አገዛዞች ጋር መቃረናችን ደግሞ የማያባራ ይሆናል፡፡ የጋራ ሀገር የለንም፤ መብታችን አልተከበረም ብለው የሚታገሉትንም  ሁሉ ኢሕአፓ የሚደግፈው ለዚሁ ነው፡፡ ትምክህትም ጠባብ ብሄርተኝነትም ሀገር አጥፊ ናቸውና ኢሕአፓ ሁለቱንም በአፍ ደረጃ ሳይሆን፥ በተጨባጭ ተቃውሞና  ከባድ መስዋዕት በመክፈል፥ ማን  በገቢር ለሀገር ለኢትዮጵያ እንደቆመ አስመዝግቧል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ፥ የአዞ እንባ የሚያነባውንና፥ የሕይወት መስዋዕት የሚከፍልለትን በሚገባ የሚረዳ ታሪካዊና ባለ ውለታ ሕዝብ ነው፡፡  ዛሬ የኢሕአፓን ሀገር ወዳድነት በጥያቄ ሊያስገቡ የሚውገረገሩትንም፥ ለመሆኑ እናንተ በዚህ መስክ ምን ሰርታችኋል? ሕዝብ ሲጨቆን ሲበደል ምን ተቃውሞ አሰምታችኋል? የት ነበራችሁ? ምን አደረጋቸሁ? ብሎ መጠየቁ የግድ ሆኗል፡፡ ከታሪክና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብያኔ ማምለጥ አይቻልም የምንለውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡

ሀገር ወዳድነትም የሀገር ሉዓላዊነትን ማስቀደምና ሀገር በባዕድ እንዳትገዛ መዋደቅን ጠያቂ ነውና፥ ለባዕድ የሚያድሩ አገዛዞች፥ የጋራ ሀገር እንዳትኖረን ያደርጋሉ፡፡ የአፄው ሥርዓት ሀገርን ለአሜሪካ፤ የደርግ አገዛዝ ሀገርን ለሩስያ፤ ወያኔ ደግሞ ላለፈው ላገደመውና ገንዘብ ለከፈለው ሁሉ አሳልፈው የሰጡ በመሆናቸው፥ ኢትዮጵያ የዜጎቿ ሀገር መሆን  አልቻለችም፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ ዕጣ ወሳኝ የሆኑት ሕዝቦቿ ሳይሆኑ፥ ሀገሬ ኤርትራ ባዩ ግብዝ፤ የሀገራችን ስም ከርስ ነው ባዮች አሳፋሪ ፍጡሮችና ባዕዳን ናቸው፡፡ ሀገርን        ከእነዚህ መቀማትና የሕዝብ ማድረግ የግድ ያስፈልጋል፡፡ በክፍፍል ላይ የተመሠረተ አገዛዝ የጋራ ሕዝባዊ ራዕይን ሳይሆን፥ ጠባብ ቅዠትን ያቀፈ ነው፡፡ የእነ መለስ ሥርዓት ከሰር መሠረቱ በዘረኝነትና ብዙሀኑን ባመግለልና በመበደል ላይ የተገነባ ነውና፥ በጋራ የጋራ ሀገር ይኑረን የሚለውን አጥብቆ ይቃረናል፡፡ ለዚህም ነው የዕርቀ ሰላም ጥሪዎችን በሞላ ሲቃወም የቆየው፡፡ በጋራ መክሮ በመግባባትና በስምምነት የጋራ ሀገርን እውን ማድረግ ለመለስ መንጋ ሊዋጥለት አይችልም፡፡ ሆዳም

በማዕድ ብቻውን መቅረብ ይወዳልና ነው፡፡ በቡድን ደረጃም ጨዋነት የጎደለው በመሆኑ ዘረኛ አቋሙ፥ የባለጌ ህይማኖት ከጅማት ይከርራል ዓይነት ሆኖበት መሻሻል መለወጥ ከቶም ተስኖታል፡፡

ኢሕአፓ ከዚህ የተለይ አቀዋም አለው፡፡ ራዕዩ፥ ያለፈውን የቂም በቀልና የቁርሾ ባህል በመተው ለጋራ ሀገር የሚጠቅም አዲስ  ምዕራፍ ይከፈት ባይ ነው፡፡እነ መለስ፥ ድንቁርና ከመጣ ሂድልን የማይሉት እንገዳ ሆኖባቸው፥ ያደቆናቸውን ዘረኛና ቂመኛ ሰይጣን አቅፈው እያዩት ወዳለው ወድቀት ቢያመሩም፥ የእነሱ መንገድ የውድቀት ጎዳና መሆኑን ማንም የሚያጣው አይደለም፡፡ ሀገር ለሁሉም ካልሆነች ለጥቂቶች ብቻ መፈንጪያ ሆና መቀጠል እንደማትችል ግልፅ ነው፡፡ ተንደላቅቀው እየ ሩ ሕዝብ ሲያለቅስ ጆሮ ዳባ ልበስ ያሉ ዛሬ ባይሆን፥ ነገ መጠየቃቸው አይቀሬ ነው፡፡ ጥያቄው በሰላም ይሆናል ወይስ ባመረረ ቁጭት ለሚለው ደግሞ መልሱ ከወዲሁ የሚሰጥ አይሆንም፡፡ የኢትዮጵያ ህፃናት ለበሽታ፤ ለረሀብና ለአሰቃቂ ኑሮና ሞት እየተዳረጉ፥ የእነ መለስ ልጆች ቅንጦት በቅንጦት ሆነው የሚንደላቀቁባት--ያውም አባታቸው የማይወዳት--አትዮጵያ፥ ከቶም በያዘችው ልትቀጥል አይታሰብም፡፡ ዛሬ ዝም-ፀጥ ያለ መስሎ የሚታየው ሕዝብ ነገ፥ ባለ ብረት እጅ የሆነውን በቀል ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ኢሕአፓ ሀገር የሁሉ ትሁን ሲል፥ በማያበቃ የበቀልና የጭቆና አዙሪት ገብተን በመተላላቅ ሀገራችንን አንደናጠፋ በማሰብ ነው፡፡ አደማኝ- ገደለኝ ከሚለው መኢሶን ጋር፥ በኅብረት ለመሰለፍ የወሰነውም፥ የሀገርን ጥቅም አስቀድሞ፤ ፍርድን ለሕዝብ ትቶ፤ ባለፈው ቁሰል ከመብከንከን፥ የዛሬን የሀገር መከራ ማስወገድ ይቀድማል በሚል ነው፡፡ ለዚህም ነው በሽብር ተሳትፈው፤ በንፁሐን ደም ተጨማልቀውና የአረመኔው አገዛዝ ካድሬ፤ሹመኛ፤ሚኒስቴርና አጫፋሪ ሆነው ከርመው  ሌባና ውሸት ወንድማማች ናቸው እንደተባለው ዛሬ በተገላቢጦሹ ያደሙትን ሊወነጅሉ ሲቧርቁ ኢሕአፓ መጥቀስ የማይፈልገውን ታሪካቸውን ከእነግሳንግሱ ማንሳት እየተገደደ ያለው፡፡ አገዛዝ በተለወጠ ቁጥር የሕዝብ ተስፋ እየተሰባባረ ፤ አንዱ ስደተኛ ሲመለስ ሌላው እየተሰደደ ፤አንዱ ከጫካ ወደ ከተማ ሲገባ፥ ሌላው ወደ ዱር እየተገፋ የሚቀጥለውን ሁኔታ፥ ኢሕአፓ ለአንዴም ለሁሌም መዝጋት-ማቆም ይመኛል፡፡ ያለውን ጨቋኝ አገዛዝ ለብቻችን አስወግደን ተክተነው የራሳችንን አመፅ ጋባዥ አገዛዝ እናሰፍናለን፤ሕዝብ የጠላውን እንመልሳለን የሚሉትንም ኢሕአፓ የሚቃወማቸው ለዚሁ ነው፡፡ ይህች ሰፊ ሀገር ለሁሉም የምትበቃና ደስታንም ልትሰጥ የምትችል ናትና በስግብግብነትና በጠባብነት ትርምስ ፈጥረንባት በደስታ ፈንታ ለቅሶነና ዋይ ዋይታን ቀጣይ እንዳናደርግባት ኢሕአፓ ታግሏል--ዛሬም እየታገለ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ምሁሮች ብሄራዊ ግዳጃቸውን ተረድተውና ከሆዳቸው ባሻገር ማየት ችለው፥ ከሀገር አጥፊዎች ጋር ሳይሆን ፥አቸናፊ መሆኑ አይቀሬ ከሆነው ሕዝብና የሕዝብ ፍላጎት ጎን እንዲቆሙ ኢሕአፓ ሁሌም ማሳሰቡን የቀጠለውም፥ ምሁሩ ክፍል ዕይታውን አሳስቶ ታሪኩን እንደያበላሽ በማሰብም ነው፡፡

ሥልጣን ለሕዝብ ሳይሆን፥ ለእኛ ብቻ ባዮች ሁሉ ሀገር አጥፊ ናቸው፡፡ እኛ ከደላን፤ እኛ ከተስማማን ሌላው ገደል ይግባ ባዮች ለሀገር አይበጁም፡፡ ኢትዮጵያ ሲባሉ በጠባቡ የሚያዩ ለሀገር አንድነት ፀር ናቸው፡፡ ለባዕድ የሚንበረከኩ የኢትዮጵያ ጠላቶች ናቸው፡፡ ሀገር ወዳድ ነን እያሉ፥ ለሆዳቸው ብቻ የሚያድሩ ጭራቆች ኢትዮጵያዊ አይደሉም፡፡ መሰል ጭራቆች ለሥልጣን ሲበቁ ደግሞ አገዛዛቸው በወንጀልና ነፍስ ግድያ ስለሚታጀብ መታረም ይከብዳቸዋል፡፡ ኮለኔል መንግሥቱ ውድቀቱ ቀርቦ ሳለም፥ ለውጥ ባደርግ የመጀመሪያው የሕዝብ ሰልፍ መንግሥቱ ይሰቀል ይሆናል ብሎ የተናገረውንና በርከታ ጄኔራሎችን ከእስር አልለቀም ብሎ ማሳረዱና ማሳነቁን እናውቃለን፡፡ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል፡፡ እነ አቶ መለስም፥ ከሚስቱ አዜብ ዶላርና ከጭፍሮቹም ዝርፊያ ባሻገር፥ በሀገረ ሽያጭና በነፍስ ማጥፋት ወንጀልም እጠየቃለሁ ብሎ ስለሚሰጋና በጀመረው መቀጠሉ ለሆዱ ስለሚመቸው ለውጥን ሆነ ንስሓን እንደፈራ መቀጠሉ አይቀሬ ሆኗል፡፡ በኢሕአፓ አስተሳሰብ ግን፥ ይህ ሁሉ ዛሬም ቢሆን ሊታረምና ሊቆም የሚችል ነው፡፡ ማንኛወም ቀን ለንስሓ አመቺ ነውና፡፡ ያለፈውንና ሀገርና ሕዝብን የጎዳውን መንገድ ትተን፥ በአዲስ መንፈስ ሀገር የጋራ ናት ብለን መነሳት አለብነ ይላል ኢሕአፓ፡፡ ለዚህም ነው ድርጅቱ መሠረት ያለወን ቁርሾውን በመተውና የሀገርን ጥቅም በማስቀደም የዕርቅና ሠላምን መንገድ ኬሌሎች ድርጅቶች ጋር በማበር የመረጠው፡፡ ኢሕአፓ በሠላም እታገላላሁ፤ በነፃ መርጫም ለመሳተፍ ዝግጁ ነኝ ሲል የደረሰበትን በደል ጭራሽ ዘንግቶ ወይም የበላይነትን ሳገኝ ቂም በቀሌን እወጣለሁ፤ በተራዬ ደግሞ እስር ቤቱን እሞላለሁ በሚል ከቶም አይደለም፡፡ በአዲስ አስተሳሰብ ለአንዴም ለሁሌም የሀገሪቷን ሰቆቃ ለማስወገድና ኢትዮጵያን የሁሉም ኢትዮጵያያ ሀገር ለማድረገ በመመኘት ነው፡፡ ኢሕአፓን ሸሽተው

የሚሰደዱ ዜጎች ጭራሽም እንዳይኖሩ ለማረጋጋጥ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግና መሀሪ ነው፡፡ በእነ መለስ ዓይነቶቹ የሚንፀባረቀውን ክፉና መጥፎ ገፅታ የሕዝብ ሁሉ አድርጎ ማስቀጠል አይፈልግም፡፡ የደም ዋጋ ከፍለን ያገኘነው ተመክሮ ሁሉ የአመለካከትና የአካሄድ ለውጥን የግድ ይላል፡፡ ይህን መረዳት አቅቷቸው ያረጀ በቅሎን ሊጋልቡ ከሚሹ ጋር ኢሕአፓ ይለያል፡፡ሕዝባችን ቂም ቢኖረውም፥ ለሀገር ሲል በቀልንም ሊተው የሚችል ሕዝብ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ ኢሕአፓም በሕዝብ እንጂ፥ በአረመኔዎች ድርጊት የሚቃኝ ሰላልሆነ፥ ሀገራችንን የጋራ ለማድረግና ለማስከበር አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ ይቀበላል፤ ያደርጋል፡፡ ሀገርን ከጥፋት አድኖ፥ የሁሉም ዜጋ ሀገር ማድረግ ከተቻለ የሚከፈለው ዋጋ ሁሉ ውድ ሊሆን አይችልም፡፡ በዚህ መንፈስ ነው ኢሕአፓ ኢትዮጵያን አስቀድሞ ከሀገር በቀልና ከባዕድ ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ሁሉ ሲታገል የቆየውና አሁንም እየታገለ ያለው፡፡ ፀረ ኢትዮጵያው የመለስ አገዛዝ ግን በጠባብና ዘረኛ ርዕዮቱ ተተብትቦ ያለ ስለሆነ ይህ የኢሕአፓ ፅኑ ሀገር ወዳድነት የሚገባው አይደለም፡፡ ሕዝብን ከፋፍሎ ፤ተቃዋሚን ደምስሶ ሊቀጥል የሚችል ይመስለዋል፡፡ የድፍድፍ ኩራቱ ውሀ እስኪገባ ነው የተባለውን የሚያውቅ አይመስልም፡፡ እነሆ እወቅ ተማር እያልነው ነን፡፡

.................................................////////////////////.....................................